# CTE ሰመር ካምፕ

Fairfax County PUBLIC SCHOOLS
ENGAGE • INSPIRE • THRIVE

እንኳን ወደ ቴክ አድቬንቸር ካምፕ ወይም CTE ሰመር አካዳሚ በደህና መጡ! **ለCTE ሰመር ካምፕ መርሃ ግብር በመመዝገብ በሚከተሉት ተስማምተዋል፡ የቤተ ሙከራ ደህንነት ህጎች፣ የዲጂታል ግብዓቶች አጠቃቀም እና የምግብ መመሪያዎች። በእነዚህ ደንቦች የማይስማሙ ተማሪዎች የደህንነት ትኩረት በሚሹ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ አይችሉም።**

## የቤተ ሙከራ ደህንነት ስምምነት

በአስተማሪ ፈቃድ፤ ተማሪዎች በእነዚህ መርሃግብሮች የሚገኙ መገልገያዎችን እና መሳሪዎችን መጠቀም ይችላሉ። የእያንዳንዱ ተማሪ የደህንነት ግንዛቤ እንዲሁም ለጥንቃቄ ህጎች ያላቸው ተገዢነት የትምህርት ክፍል ጊዜን እና የቤተ ሙከራ አካባቢን ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው። በጥቅም ላይ ለሚውሉ ለሁሉም መገለገያዎች እና መሳሪያዎች የደህንነት መመሪያ ይሰጣል። ተገቢዎቹን የደህንነት መመሪያዎች መረዳት እና መከተል ለተማሪዎ(ዎችዎ) የቀረቡትን የመማር እድሎች ያግዛል። ተማሪዎች ለሚከተሉት ህጎች ተገዢ መሆን አለባቸው።

1. በቤተ ሙከራ ውስጥ ሁልጊዜ የአይን መከላከያ መነፅር ማድረግ
2. በልክ ያልሆነ ልብስን ማስወገድ ወይም ማስተካከል እና እጅጌዎችን ከክርን በላይ መሰብሰብ
3. በቤተ ሙከራ ውስጥ ሲሆኑ የእግር ጣቶችን የሚሸፍን ጫማ ማድረግ
4. በአስተማሪ እንደተገለጸው የመከላከያ ልብሶችን መልበስ
5. ረዥም ፀጉርን ወኋላ ማሰርር ወይም አስፈላጊ ከሆነ ኮፍያ ማድረግ
6. በመሳሪያ ደህንነት ህግ እንደተጠየቀው ጌጣጌጦችን ማውለቅ
7. ስለታማ/ሹል የሆኑ መሳሪያዎችን ከእራሳችሁ እና ከሌሎች በተቃራኒ ወደ ታች አድርጎ መያዝ
8. አጠቃቀሙን ካላወቃችሁ በስተቀረ ምንም አይነት መሳሪያ አለመጠቀም፤ እርግጠኛ ካልሆናችሁ አስተማሪያችሁን መጠየቅ
9. ወዲያውኑ ተጠቅማችሁ ስታበቁ፤ መሳሪያዎችን እና ቁሳቁሶችን ወደ ተገቢ ቦታቸው መመለስ
10. ሁሉንም የተለጠፉ የመገልገያ፣ የመሳሪያ እና የደህንነት ቦታ ህጎች መከተል
11. አስተማሪው/ዋ የመሯችሁን እና እንድትተቀሙ መመሪያ እና ፈቃድ የሰጧችሁን መሳሪያ ብቻ መጠቀም።
12. ለደህንነት አስጊ የሆኑ ሁኔታዎችን፣ ብልሽት ያጋጠማቸውን እና የዶለዶሙ መሳሪያዎች በተመለከተ ወዲያውኑ ለአስተማሪያችሁ ማሳወቅ።
13. የጉዳቱ መጠን ምንም ይሁን ምንም፤ ሁሉንም አደጋዎች ወዲያውኑ ለአስተማሪያችሁ ማሳወቅ።
14. ወሳሪያዎችን በመጠቀም ላይ ያሉን ተማሪዎች ከማዋራት ወይም ከማዝናጋት መቆጠብ።
15. በቤተ ሙከራ ውስጥ ከመሮጥ፣ እቃዎች ከመወራወር፣ አላስፈላጊ ድምጽ ከማሰማት መቆጠብ።

ማስታወሻ: ማንኛውም በትምህርት ክፍል እና በቤተ ሙከራ  አካባቢ ያሉ መገልገያዎችን ምክንያት ያደረገ ጠብ ከትምህርት ቤት እና የቤተሙከራ አካባቢ ያስባርራል። ማንኛውም መገልገያ እንደ ማጥቂያ መሳሪያ ይቆጠራል! ተመላሽ አይኖርም

**የኢንተርኔት ላይ/ዲጂታል መገልገያዎች አጠቃቀም**

**ይህ ደብዳቤ የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግን (FERPA) በማክበር ወደ ቤት የተላከው፤ FCPS ዲጂታል መሳሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የተማሪን መረጃ ለመጠበቅ ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች መረጃ ለመስጠት ነው። ይህን ቅጽ በመፈረም ልጅዎ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በFCPS የጸደቁ የኢንተርኔት ላይ መገልገያዎች እንደማስተማሪያ ፕሮግራም አካል እንዲጠቀም ፍቃድ ሰጥታችኋል።**

ፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን ትምህርት ለማገዝ የተለያዩ መገልገያዎችን ይጠቀማል። FCPS ከሻጭ ጋር የተማሪ መረጃን ለማስተናገድ በሚዋዋልበት ጊዜ፣ FCPS ሻጩ በውላቸው ውስጥ በተካተቱት የሚስጥራዊነት ስምምነት ውስጥ የተገለጹትን የደህንነት እና የግላዊነት መስፈርቶች እንዲያከብሩ ይፈልጋል። FCPS ከእያንዳንዱ የማስተማሪያ መገልገያ አቅራቢ ጋር ውል የለውም። በርካታ ጠቃሚ የማስተማሪያ መገልገያዎች በአገልግሎት ውል (TOS) የሚተዳደሩ ናቸው፤ እንዲሁም ሁለቱንም፡ ነጻ እና የሚከፈልባቸው መገልገያዎችን ያካትታሉ። ልጅዎ በዚህ አመት ሊጠቀሙባቸው ከሚችሏቸው አንዳንዶቹ ዲጂታል ግብዓቶች የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።

መምህራን በCTE Summer Camp ውስጥ [FCPS Digital Ecosystem Library](https://del.fcps.edu/) (https://del.fcps.edu/) ላይ የሚገኙትን ማናቸውንም ዲጂታል መሳሪያዎች ለመጠቀም መምረጥ ይችላሉ። ከእነዚህ መገልገያዎች ውስጥ አንዳንዶቹ የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።

መሳሪያዎቹ ከFCPS የመማሪያ ሞዴል ጋር መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ በጥንቃቄ ተገምግመዋል፤ እንዲሁም FCPS ለሁሉም የተማሪ መረጃን ለሚጠቀሙ ሁሉም ምርቶች ተመሳሳይ የቴክኒክ ግምገማዎችን ያካሂዳል። እነዚህ አካላት በፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች ውስጥ የተካተቱትን ጨምሮ፤ በሚመለከታቸው መተግበሪያዎች ላይ የተፈጠሩ ማናቸውም የተማሪ ስራዎችን በማካተት፤ በእነሱ ብቻ ሳይወሰን፣ ተግባራቸውን ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑትን ከልጅዎ የትምህርት መዝገብ የተወሰኑ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

በልጅዎ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ የተለዩ መገልገያዎች መረጃ ለማግኘት እባክዎ ቤት ሜርን/Beth Mehr ያነጋግሩ። ተጨማሪ መገልገያዎች ወደዚህ ዝርዝር ከተጨመሩ እና የወላጅ ፍቃድ ወደሚፈልጉ መገልገያዎች መርጠው የመግባት እድል የሚሰጡ ማሳወቂያ ይደርስዎታል። በተጨማሪም፣ FCPS ማንኛውንም የግል መረጃ የማይሰበስቡ፣ የማይጠቀሙ ወይም የማያጋሩ ዲጂታል መሳሪያዎችን ሊጠቀም ይችላል።
FCPS ስለ ለተማሪ ግላዊነት ያለውን ቁርጠኝነት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ።
[https://www.fcps.edu/resources/technology/digital-citizenship-internet-safety/digital-privacy-fcps](https://www.fcps.edu/resources/technology/digital-citizenship-internet-safety/digital-privacy-fcps) እንዲሁም ስለ አቅራቢዎቹ የግላዊነት ማሳወቂያ እና ሌላ ጠቃሚ መረጃ አገናኝ የያዘ ሁሉም የፀደቁ ዲጂታል መሳሪያዎች ዝርዝር በኢንተርኔት ላይ በ [FCPS Digital Ecosystem Library](https://del.fcps.edu/) (https://del.fcps.edu/) ላይ ሊታይ ይችላል።

ይህ ፈቃድ በሰመር የመማሪያ ፕሮግራም መጨረሻ ላይ ጊዜው ያልፍበታል።
ለCTE ሰመር ካምፕ ፕሮግራም በመመዝገብ፣ ተማሪዎ በFCPS እውቅና የተሰጣቸው ዲጂታል መገልገያዎችን እንዲጠቀሙ ፈቃድ እየሰጡ ነው።

**የምግብ ስምምነት**

አንዳን ትምህርቶች የምግብ አሰራር ጥበብን እንዲቃኙ ይፈቅዳሉ ፡፡ በምዝገባ ሂደቱ ወቅት ተማሪዎ ሊኖራቸው የሚችለውን ማንኛውንም እና ሁሉንም ምግብ ነክ ስጋቶችን እንዲለዩ ይጠየቃሉ። ተማሪዎን በማስመዝገብ የምግብ አለርጂዎችን ወይም ስሜቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉ የምግብ አሰራር አስተማሪዎች እንዲያገኙዎት ፍቃድ ይሰጣሉ።

አስተማሪዎች መረጃውን አለርጅይ ምልክቶች የሚታይባቸን ሁነታዎች ለመቀነስ የምግብ አይነት ማዘጋጃ ይተቀሙበታል ፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ተማሪዎ ለአለርጂ እንደማይጋለጡ ዋስትና ልንሰጥ አንችልም። **እባክዎ አለርጂዎችን በተመለከተ ከልጅዎ ጋር ይነገሩ፤ እንዲሁም ማንኛውንም አለርጂ ሊያስከትል የሚችል ምግብ ከመብላት እንዲቆጠቡ ያበረታቷቸው።**

ለCTE ሰመር ካምፕ መርሃ ግብር በመመዝገብ በቤተ ሙከራ ደህንነት ህጎች እና የምግብ መመሪያዎች ተስማምተዋል። በተጨማሪም፣ የደህንነት ትኩረት በሚጠይቁ ክፍሎች ውስጥ ተማሪዎ መሳሪያዎችን እና መገልገያዎችን እንዲጠቀሙ ፈቃድ ሰጥተዋል ፡፡ የምዝገባ ሂደቱን ማጠናቀቅ የቤተ ሙከራ ደህንነት እና የምግብ አሰራር ህጎችን ከተማሪዎ ጋር እንደገመገሙ እና ተማሪዎ ተጨማሪ የደህንነት እርምጃዎችን የሚሹ መገልገያዎችን እና መሳሪያዎችን እና እንደሚጠቀሙ እርስዎ እንደተገነዘቡ ያሳያል። በተጨማሪ ለምግብ ስራ አስተማሪ የምግብ አለርጂ ወይም አለምስማማት ጥያቄ ወይም ስጋት ካለ እንዲያገኛችሁ ፈቃድ ሰጥታችኋል።

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ Beth Mehr የ CTE የትምህርት ባለሞያን፣ በኢሜይል (bgmehr@fcps.edu) ወይም በስልክ (571-423-4161) ያግኙ።